# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**የከቲት 10 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**መለስ ስርዓቱ በሙስና የነቀዘ መሆኑን አመነ ፤**

**ከተለያዩ ወገኖች ተቃውሞ ደረሰበት**

**መድረክ በሊዝ ጉዳይ ላይ የአዳራሽ ውስጥ ሕዝባዊ ስብሰባ አከሄደ፤**

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለፈው ሳምንት ባቀረበው ሪፖርት ዙሪያ የህዝቡ ስሜት ምን ይመስላል ተብሎ በደህንነቶች እንዲጠና የተደረገ ሲሆን ከተለያዩ አቅጣጫዎች ደግሞ ከፍተኛ ትችት እና ተቃውሞ እየቀረበበት መሆኑ ታወቀ::

ባለፈው ሳምንት ሐሙስ የካቲት 1 ቀን 2004 ዓ.ም የስድስት ወራት ሪፖርት በሚል ለፓርላማ ባቀረበበት ወቅት የወቅቱን የሀገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበና ያላካተተ በመሆኑ የተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች ከፍተኛ ተቃውሞ እና ወቀሳ እየሰነዘሩበት መሆኑ ታውቆዋል::

በአሁኑ ሰዓት በሀገሪቱ ውስጥ እጅግ አነጋጋሪ እና አነታራኪ የሆነው የሊዝ አዋጁ ላይ እንዲሁም በዋጋ ግሽበቱ ዙሪያ ሰጠ የተባለው ማብራሪያ ፍጹም ተዓማኒነት የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ የወቅቱን የሀገሪቱን ተጨባጭ እውነታ ፍጹም ያላገናዘበ የፈጠራ ወሬ ነው ሲሉ አንዳንድ ወገኖች እየተቹት ይገኛሉ::

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የሚመራው መንግስት እጅግ የተዳከመ በመሆኑ የራሱን ካድሬዎች ጭምር መቆጣጠር አቅቶት እየተዝረከረከ መሆኑን በግልጽ እየታየ ነው በማለት እነዚህ ወገኖች እየገለፁ ይገኛሉ::

እንደ እነዚህ ወገኖቸ ትችት እና ተቃውሞ ከሆነ መለስ ለ21 ዓመታት የመራው መንግስት የሌባ ጥርቅም መሆኑን በይፋ ከመናገሩም በላይ ሀገሪቱን እና ህዝቡዋን ለድህነት እና ለምድረ በዳነት የዳረገ በመሆኑ በዓለም አቀፍ ህግ ሊጠየቅ ይገባል ሲሉም አጽንኦት ሰጥተው ገልጸዋል::

መለስ ከዚህ ቀደም መሐይምም ቢሆን ዘበኛ የፖለቲካ ወገንተኝነት ካለው ሚኒስትር ሆኖ የማይሾምበት አንዳችም ምክንያት የለም ብሎ የነበረ ቢሆንም ሲሾማቸው የነበሩት ግን በጠቅላላ ሌቦች እና የሀገር ሀብት ዘራፊዎች መሆናቸውን በራሱ አንደበት መናገሩ ከተጠያቂነት እንደማያድነው ምሁራኖች በቁጭት እና በንዴት እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡

የወያኔ አባል እና አጨብጫቢ ስለሆኑ ብቻ ምድረ ሌቦችን ብቃት አላቸው እያለ ሲሾም የነበረው መለስ ዜናዊ ዛሬ የሀገሪቱ ሀብት ተግጦ ካለቀ በሁዋላ ለሀገር አሳቢ በመምሰል ሌባ እያለ የራሱን ሹመኞች ቢሳደብም ዋነኛው ሌባና አጭበርባሪ እራሱ መሆኑን መዘንጋት የለበትም እያሉ የሚተቹት እና የሚቃወሙት ወገኖች ዛሬ በሀገሪቱ የመልካም አስተዳደር እጦት......ሙሰኝነት መንገሱ.....የኑሮ ውድነቱ መባባሱ ዋነኛው መንስኤ እራሱ የፈጠረው ችግር መሆኑን በሪፖርቱ ላይ በይፋ መግለፁ ከተጠያቂነት ሊያድነው እንደማይችል እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡

ሌሎች ደግሞ የተቃወዋሚ ድርጅቶች መሪዎችን ጨምሮ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ስርዓቱ በሌቦች መጨማለቁን አምኖ ቢናገርም መቀጣታቸውን እና የሚቀጡበትን መንገድ በግልፅ ይፋ አለማድረጉ ወንጀለኛን እብብቱ ስር ሸሽጎ ግመል ሰርቆ አጎንብሶ እንደመሄድ ያስቆጥርበታል ሲሉም ይገልጻሉ፡፡

መለስ ዜናዊ እያደረገ ያለው የጠገበውን መዥገር አንስቶ የተራበውን መዥገር መመደብ ነው ያሉት እነዚህ ክፍሎች ዛሬ በሀገሪቱ ስር የሰደደ ርሀብ እና እርዛት እያለ ምንም እንዳልተፈጠረ ከማስመሰሉም በላይ እራሱ ከህዝብ ዝረፋ ያላቸውን ሌቦች መልሶ መሳደቡና ማጋለጡ አሁንም በህዝብ ላይ ከማላገጥ የዘለለ አይሆንም ሲሉም ይተቻሉ፡፡

መለስ ዜናዊ 21 ዓመት ሙሉ ሀገሪቱዋን ሲያስመዘብር እና ሲያዘርፍ ከርሞ ዛሬ ደርሶ ለሀገር እና ለህዝብ ተቆርቁዋሪ ለመምሰል ሌባ እያለ መናገሩ ቢያስገርምም የሀገሪቱ ሀብት ሲጋጥ የነበረው በራሱ መሪነት እንደሆነ ማንም የሚያውቀው ሀቅ ነው ሲሉም ይተቻሉ፡፡

የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊን ጨምሮ ባለስልጣናቱ ህዝቡን ምን ያመጣል ብለው ስለናቁ ምንም ዓይነት ውይይት ሳይደረግበት የሊዝ አዋጁን ከማውጣታቸውም በላይ አዋጁን አልቀበልም እያለ የሚቃወመውን ዜጋ የልማት እንቅፋት በሚል ታፔላ እየለጠፉበት ወደ እስር ቤት ማጎር መጀመራቸው የመጨረሻቸው መጀመሪያ ላይ መድረሳቸውን ያመላከተ እርምጃ ነው ሲሉም እነዚሁ ወገኖች ያስጠነቅቃሉ፡፡

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ ግዙፍ ባለሀብት እየሆኑ በዘመዶቻቸው ስም የንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ጭምር የገቡት የወያኔ ባለስልጣናት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን በተለይ አዜብ መስፍንን ጨምሮ ከፍተኛ ባለስልጣናት ከመንገድ ስራ ተቁዋራጭ እስከ እርሻ ልማት.....ከሪል እስቴት ግንባታ እስከ መኪና አስመጪና ሻጪነት......ስራ ላይ ተሰማርተው የነጋዴውን የስራ ድርሻ ቀምተው እና ተቀራምተው እየሰሩ ያሉ መሆኑን በግልጽ የሚያውቀው መለስ ይሄንን ለመናገርና ለማውጣት ወኔ

በማጣቱ በድፍኑ ሌባ ሌባ እያለ ሲለፍፍ መዋሉ ከተጠያቂነት እንደማያመልጥም በግልጽ ሊያውቀው ይገባል ሲሉም እየተናገሩ ይገኛሉ::

መልካም አስተዳደር በሀገሪቱ በመጥፋቱ እና ሙስና በመስፋፋቱ ሀገሪቱ ቁልቁል እንደካሮት እየተቀበረች ከመሆኑም በላይ ዛሬ ዜጎች የሚልሱት የሚቀምሱት አጥተው በየጎዳናው ላይ በርሀብ እየሞቱ ያለበት ሰዓት መሆኑን የዓለም አቀፍ መገናኛ ብዙሀን ጭምር በምስል እያስደገፉ እየዘገቡ ቢሆንም ርሀብ ምን እንደሆነ የማያውቁት የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ግን በውስኪና በጮማ እየተምነሸነሹ ይገኛሉ ያሉት የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ሰሞኑን ለይምሰል ያህል የወረዳና የጥቃቅን ከተማ ከንቲባዎች በሙስና እየተባሉ መታሰራቸው ስርዓቱና መለስን ከተጠያቂነት ፈጽሞ ሊያድናቸው እንደማይችልም ይናገራሉ::

በፍርሀት ተወጥሮ ያለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ በበኩሉ ሰሞኑን ባቀረበው የግማሽ ዓመት ሪፖርቱ ዙሪያ ህዝቡ ምን ይላል የሚል ክትትል እንዲያደርጉ እስከ ጎጥ ድረስ ያሉ ደህንነቶች ተሰማርተው ወሬ ሲቃርሙ እንደሰነበቱ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

ከብሔራዊ መረጃ እና ደህንነት ቢሮ በወጣ መመሪያ እና ትዕዛዝ የደህንነት ሰራተኞች እና የወጣት ፎረም አባሎች ከቀበሌ እስከ ጎጥ ድረስ ወርደው የህዝቡን ሁኔታ አጥንተው ሪፖርት እንዲያደርጉ ታዝዘው የነበረ ሲሆን በዚሁ መሰረት ጥናቱን ማቅረባቸውን የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ደህንነቶች ባደረጉት ጥናት ህዝቡ በመለስ ሪፖርት እጅግ ከመበሳጨቱም በተጨማሪ መዘኑንና ማኩረፉን  ለመለስ ሪፖርት እንደተደረገለት የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በዚህም ምክንያት መልሶ እስከ ቀበሌ ድረስ ያሉት ካድሬዎች ህዝቡን እየሰበሰቡ የማሳመን ስራ እንዲሰሩም አዲስ ትዕዛዝ መሰጠቱ ታውቆዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ  መድረክ የተባለው ድርጅት በቅርቡ በወጣው የሊዝ አዋጁ ዙሪያ ከህዝብ ጋር ለመጀመሪያ ግዜ በአዳራሽ ውስጥ መምከሩ ታወቀ::

እሁድ የካቲት 4 ቀን 2004 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ ቄራ አካባቢ በሚገኝ ህዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ባደረገው ህዝባዊ ምክክር ላይ በሺህዎች የሚቆጠሩ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የተገኙ ሲሆን ተሰብሳቢዎቹ ያለ አንዳች ፍርሀት ስሜታቸውን ሲገልፁ እንደነበረም ተዘዋወሪ ዘጋቢያችን አረጋግጦዋል::

እንደ ዘጋቢያችን ገለጻ ከሆነ በዚሁ ለመጀመሪያ ግዜ በተደረገ የህዝባዊ ስብሰባ ላይ ህዝቡ በወያኔ ላይ ያለውን ጥላቻ በይፋ የገለጸበት ከመሆኑም በተጨማሪ በቅርቡ ባወጣው የሊዝ አዋጅ ላይ የተለያዩ የቁጣ መልእክቶች  ማስተላለፋቸውን ገልጾዋል::

በተለይ በእድሜ ጎልማሳ የሆኑት ብዙዎቹ ተሰብሳቢዎች ወያኔ በተለያየ ግዜ የተለያዩ አሳሪና ቀፍዳጅ ህጎችን እያወጣ መላወሻ መተንፈሻ ከማሳጣቱም በላይ አሁን ደግሞ የሊዝ አዋጅ ብሎ ጭሰኛ ሊያደርገን መቁዋመጡ አሳፋሪና አሳዛኝ ከመሆኑም በተጨማሪ ሚስቶቻችንን በሊዝ ስም ሊነጥቀን መዘጋጀቱን ያሳየ ነው ሲሉ በእልህና በቁጭት ሲገልፁ እንደነበር ዘጋቢያችን ገልጾዋል::

በዚሁ በተደረገ ህዝባዊ ውይይት ላይ የመድረክ አመራሮች የተገኙ ሲሆን እነሱም አዲሱን የሊዝ አዋጅ መርዝ ያለበት ወተት ሲሉም በፅኑ አዋጁን መቃወማቸውን ለተሰብሳቢዎቹ ይፋ አድርገዋል፡፡

የወያኔ ባለስልጣናት በወረቀት የህዝብን ሀብት የሆነውን መሬት ሲቸበችቡ መክረማቸውንና በሞተ ሰው ስም ጭምር መሬት በመሸጥ ገንዘብ አግበስብሰው ቢሊየነር እንዲሆኑ የተደረገ ሲሆን ሁሉም ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በሁዋላ ህዝቡን ጨርሶ ደሀ ለማድረግ እና ተገዥ ለማድረግ አዋጁን ማውጣታቸውንም አጋልጠዋል፡፡

በስብሰባው ላይ የነበሩት ተሳታፊዎች በበኩላቸው ወያኔ ያወጣው አዲሱ ለድህነት እና ለባርነት የሚዳርገው የሊዝ አዋጅ ስጋት እንደፈጠረባቸውና ወያኔም እንዳሻው ከህዝብ ፍላጎት ውጭ አዋጅ ማውጣት ስለማይችል ይብቃህ ልንለው ግዜው ግድ ይለናል ሲሉም ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡